# <u>እንደራጅ!!</u>

እናት ኢትዮጵያ ጡቷን ስታጠባ
ንክሰ ቡጭቅ አርጎ በደም ለሚቀባ
ለወያኔ እድሜ ሲያሴሩብን ደባ
ሌላም በተገባ አይደለም እቀባ፡፡
ጭራሽ አፈንግጠው ከመሪያችን ቃል
ሕገ ደንቡን ጥሰው እንዲያው መፋለል
“ይበቃል!” ከእንግዲህ ሕዝቡ ተቆጥቷል!

አሜሪካ መጥተው ሲዘሉ፣ሲረግጡ
የኢትዮጵያኑን ገንዘብ ሰብስበው ሲሮጡ
ዝም በሉ ይሉናል፣ አታንሱ ስለአገር
በሀሰት በውሸት ወገን ሲደናገር
ለጠላት ተገዝተው ሲጭኑብን ቀንበር፡፡
ሚዲያውን ገዝተው፣ አፈኛውን ይዘው
የስድብ ድሪ ገጽ፣ ፓልቶክ ክፍል ከፍተው
ጀግናውን ተጋፍተው አገር ወዳድ ሰድበው
የወያኔን ስራ ተቃዋሚ መስለው
ሲሰሩ አየናቸው እኛን መስለው ገብተው፡፡

የተሰረቀውን የህዝብ ድምፅ ረስተው
የጋራ አመራር መፈክር አንግተው
ሕዝብ የመረጠውን መሪያቸውን ትተው
ይደናበራሉ በጭፍን ተመርተው
ከእንግዲህስ ጠፍቷል ጨረሩ የብርሃኑ
ሁሌም ይኖራሉ በቁም ሲባንኑ፡፡

የአንድነት ኃይሉ ነቃ ብለህ ታገል
ከወያኔ አገዛዝ ህዝብ እንዲገላገል፡፡
በምን አበሳዋ እናት ጥቁር ትልበስ
የወለደችው ልጅ በጥይት ሲጠበስ
ሌላዋ ታስራባት ስንቅ ስታመላልስ
ጀግና አያሳጣት እምባዋን የሚያብስ፡፡

ከድቶ የሚያስከዳ ለጥቅሙ ሲቀይስ
በአምስት መቶ ካሬ የምን መለሳለስ!?
ያንተው አይደለም ሲወርድልህ መለስ
በራስህ ንብረት ሸጠውልህ መሬት
ወያኔን ማር አትበል እየሆነ እሬት።

ፍንትው ብሎ ጠርቷል የትግላችን ጎራ
የአንድነት ኃይሉ መጥቷል እየመራ
የታጋዮች ድካም ፍሬው እስኪጎመራ
ከኃይሉ ጋር መቆም ምን ቢሆን መራራ
ከዚያ በላይ የለም ለሀገር የሚያኮራ ።

እንፍጠር አንድነት፣ ባለንበት ቦታ
ሁለትም ሶስት ሆነን ምንም አናመንታ
እንንቃ እንደራጅ፣ እኛም ባለንበት
በዋዛ ፈዛዛ ጊዜው አይለፍ በዘበት

ሰብሰብ ማለት ነው በኢትዮጵያዊነትህ
በአንድነትህ ፅና፣ ቁም ለሰብዓዊ መብትህ
በእድር ይሁን በእቁብ ወይንም በማህበር
ስለአገርህ ጠይቅ ተወያይ ተማከር
ወያኔ የሚፈራው የኛን መሰባሰብ
ወገኔ እንነሳ ሳናበዛ ሰበብ።
ዛሬ ነገ እያልን ጊዜያችንን ሳንፈጅ
በኢትዮጵያዊነት ጸንተን እንደራጅ።

ከሚካኤል ሰይፉ ( ቶሮንቶ፤ ካናዳ)